# ምዕራፍ አስራ አንድ

### ለፍፃሜው ዝግጅት፣ የቴዎድሮስ የመጨረሻ 30ሺ ተፋላሚዎች፣ ከባድ መሳሪያ ድብደባ፣ መቅደላ መግቢያ በር ላይ፣ መቅደላ ላይ የንጉሰ ነገሥቱ ራሳቸውን ማጥፋት

ሚያዝያ 13፣ 1868 በፋሲካ ማግስት፣ ሰኞ ጠዋት፣ ኩሩዎቹ የፋላና የሰላሴ ኮረብታዎች በፀሀይ ብርሃኑ በድምቀት ወገግ ብለዋል፡፡

በቀጥታ የመቀስቀሻው ጥሪ ተሰማ፣ ጥሩምባ ሲነፋና ከበሮው ሲመታ፣ የሚርመሰመስ ሕይወት መንቃት ጀመረ፡፡ ወታደሮቹ ከድንኳኖቻቸው ፊት ለፊት ራሳቸውን ያንቀሳቅሱ ጀመር፤ ብዙዎቹ እያዛጉና እየተረመረሙ፣ ሳቅና ቀልደም ይቀላቅሉ ነበር፡፡ የየኮምፓኒው ወታደሮች በየክፍላቸው ተሰለፉ፤ ስም ቆጠራ ተጀመረና ሲጠሩ መልስ ከሰጡ በኋላ ሰልፉ ተበትኖ ወደ ቁርስ ገበታቸው አመሩ፡፡

ከጥዋቱ ሁለት ሰአት ሲሆን፣ በፋላ ቁልቁለት፣ ስምንት የአቢሲኒያ ሰዎች መጡ፤ የተለያዩ ከፍተኛ ማዕረግ ያላቸው፣ ከሐር የተሰራ ቀሚስ እንደለበሱ፣ ፀጉራቸው እንደየምርጫቸው ተንጨባርም ሆነ ተጎንጉኖ፣ እንገታቸው ላይ ከበድ ያሉ ጌጦች እንጠልጥለው፣ ደረታቸው ደግሞ በብር ሜዳሊያዎች ተንቆጥቁጧል፡፡ ወደ ሰር ሮበርት ድንኳን እንዳመሩ ወዲያውኑ፣ ዙሪያውን በወታደሮች ተከበቡ፡፡ ወታደሮቹ የተጠሩት ሥርአት እንዲያስጠብቁና ለውይይት ክፍት ቦታ እንዲፈጥሩ ነበር፡፡

የእንግሊዙ ጦር አዛዥ እንደቀረበ ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ፣ በአስተርጓሚያቸው በአቶ ሳሙኤል (በንጉሡ ተወዳጅ) በኩል ሃሳባቸውን አቀረቡ፡፡ ሃሳባቸው፣ ፋላና ሰላሴን ለማስረከብ እንደመጡ ነው፤ ያ ግን የሚሆነው ምንም ሳይደረጉ ለቀው መሄድ ሲፈቀድላቸው ብቻ ነው፡፡ ጥያቄያቸው በሰር ሮበርት ተቀባይነት ስላገኘ፣ በጥያቄያቸው መሰረት ወደየቤታቸው ሲሄዱ በሽሎን እስከሚያቋርጡ ድረስ እሱ ራሱ ሲጠብቃቸው ቃል ገባላቸው፡፡

ስለ ንጉሰ ነገሥቱ ሲጠየቁ፣ አለቆቹ ሲመልሱ፣ ከመጨረሻው የናፒየር ጥሪ በኋላ ቴዎድሮስ ጥለው እንደሄዱ ነው የገለፁት፡፡ ይህ እንግዲህ ወደ አኩለ ሌሊት አካባቢ መሆኑ ነው፡፡ እንደ አባባላቸው፣ ቴዎድሮስ ወይ ወደጎጃም ሄደዋል፤ አለዛም ወደንግስት መስታውት የኦሮሞ ካምፕ ሄደዋል፡፡ ምንም እንኳን ንግስቲቱ የሰውየው ደመኛ ብትሆንም፣ በእስልምና ደንብ

መሰረት በአሷ ካምፕ ውስጥ እስካሉ ድረስ የንጉሡ ህይወት የተጠበቀ ነው የሚሆነው፡፡

ይህ ነገር፣ ጄኔራል ናፒየር በፍፁም ያሰበው ወይም ያለመው አልበረም፡፡ ቴዎድሮስ፣ በመቅደላ ጀርባ መልካጨሎ በሚባል፣ ከበሽሎ ጋር በትይዩ በሚወርድ ስፍራ ያዘጋጀውን የፈረሰኛ ከበባ አምልጦ መሄድ ይችላሉ ብሎም አሰበ፡፡ ወዲያውኑም፣ ቴዎድሮስን በህይወት ላመጣ ወይም ለገደለ ሰው 50ሺ ዶላር ሽልማት እንደሚሰጥ አወጀ፡፡ ይህን አዋጅ ይዘው፣ መልከተኞች ወደ ዋግሹም ጎበዜ[135] ካምፕ፣ ለሙስሊም ኦሮሞዎች ንግስት መስታውትና ለአዘቦ ክርስቲያን ኦሮሞዎች ንግስት ወደ ወርቂት ተላኩ፡፡

ሰር ሮበርት፣ ቀጥሎም፣ ፋላና ሰላሴ እንደተያዙ ራሱን በነዚህ ምሽጎች ካጠናከረ በኋላ ወደ መቅደላ ለመቀጠል ወሰነ፡፡ ሰር ቻርልስ ስታቨሊም ከፋላ ግርጌ ባለው ሜዳ ላይ ጦሩን እንዲያሰልፍ ታዘዘ፡፡

በወታደሮቹ አካባቢ የመነቃቃት ሁኔታ ይታይ ነበር፤ በመኮንኖቹ አካባቢ ደግሞ ብዙ ወሬ ይወራል፤ አሽከሮችና የህንድ ፈረሰኞች ፊታቸው ላይ የመደነቅ ስሜት ይታያል፡፡ ይህ የውጊያው የወደፊት ዜና በዚህም በዚያም በጋለ ሁኔታ ሲወራ በሰዎች ላይ የሚነዝር ስሜት ነው የፈጠረው፡፡

በዘመቻው የታለመው ትልቁ ውጤት ሊከናወን ነው፤ እናም ሁላችንም የተንገላታንበት ይህ ውጤት ወደ ፍፃሜው እየተቃረበ ነው፡፡

ከዚያም፣ እያንዳንዱ ሬጅመንት ትዛዙን ሲያስተጋባ፣ የጥሩምባዎች ጩኸት በተከታታይ መሰማት ጀመረ፤ የእነዚህን የጥሩምባ ድምፅ ደግሞ፣ ግራጫ መልከ፣ ስፋትና ግርማ ሞገስ ያላቸው ኮረብታዎች በማስተጋባት ራቅ ባሉ የተራራ ሰንሰለቶች ድረስ እንዲሰሙ አደረጓቸው፡፡ ከዚያ ቀጥሎ፣ ከበሮዎች ሲመቱ፣ ትራምፔቶች ሲነፉ፣ ኮሰተርና ቀጥ ያሉ ወታደራዊ ትዛዞች፣ በመጨረሻም ሬጂመንቶቹ በአራት ረድፈ ተሰልፈው በጥቂት ሙዚቀኞች እየተመሩ ወደ ፋላ ሜዳ መንቀሳቀስ ጀመሩ፡፡

33ኛው የአየርላንድ ሬጅመንት (የዌልንግተኑ መስፍን ጦር)፣ በነበራቸው ጥሩ ባሕሪና፣ የሚያሳፍር ትውስታ ከተፈጠረበት ዲልዲን ከለቀቁ በኋላ ባሳዩት ትዛዝን በፍጥነት የመቀበል ሁኔታ ለግዳጁ ተመረጡ፡፡ ወታደሮቹም በ "ያንኪ ዱድል" ሙዚቃ በሚያነቃቃ ፈጣን ርምጃዎች ሰልፋቸውን ቀጠሉ፡፡ ይህ ሬጀመንት፣ በዚህ በሶስት ምሽቶች በሚደረገው ድራማ በመጨረሻው

---

135 ዋግሹም ጎበዜ ወደ እንግሊዞች ካምፕ ባይመጡም፣ አንታቸውን ደጃዝማች መሸሻን የወከሉ መሆናቸውን ለእንግሊዞቹ ገልጠዋል፡፡ ደጃዝማቸ መሸሻ፣ ቴዎድሮስ አምልጠው እንዳይሄዱ አምባ ኮሂት የሚባል ቦታ ይዘው እንዲጠብቁ በናፒየር ታዘው ነበር፡፡

ክፍል ወሳኝ ሚና ለመጫወት የተመደበ ነው። የእጥቂውን ጦር የሚመራው ይህ ክፍል ነው።

በዚህ ቀን፣ ሬጂመንቱ የሚያደርገው እንቅስቃሴ በአዛዡ ቅርብ ክትትል እንደሚደረግበት ያውቃል። አካሄዳቸውና ሁኔታቸው በሙሉ፣ "እታስቡ፣ ውጊያና ሰልፍ የተለያዩ መሆናቸውን እናሳያችኋለን፤ በአለም ምርጥ ተዋጊ ሬጅመንት ተብሎ የሚታወቀውን ዝናችን ተግባራዊ ለማድረግ እንጥራለን።" የሚል ይመስላል።

33ኛውን አግረኛ ተከትሎ፣ ባንዱ "ጌሪ እውን" እየተጫወተ፣ እራተኛው የንጉሡ የሚባለው ሄደ። ቀጥሎም 45ኛው (የአውሮፓውያኖቹ)፣ ባንዱ "ቺር ቦይስ ቺር" እየተጫወተ፣ አለፈ። ከነዚህ በጣም በታጠቁ ምርጥ፣ ቁጥራቸው ወደ 1600 የሚሆኑ የአውሮፓውያኖችን ጦር ተከትሎ፣ የሴፖይ ሬጅመንት፣ 800 ሰው ያለበት የቤሉቺዎች፣ 800 ሰው የያዘው የፑንጃቦች፣ ሁለት የ10ኛው የህንዶች አግረኛ ኮምፓኒዎች፣ መሐንዲሶችና ቆፋሪዎች፣ ተከትሎም የኮሎኔል ፔን የተራራ ከባድ መሳሪያ ከሁለት ሞርታሮች ጋር በተጨማሪ የሮኬቶች ክፍል የባህር ሀይሉ ብርጌድ ቀጠለ። የፈረሰኛው ክፍል፣ ከ3ኛው ቀላል የተወላጆች(ህንዶች) ሁለት ኮምፓኒዎች ነበሩ። የ3ኛው ድራጎን ዘቦች ደግሞ ቴዎድሮስ እንዳይሸሹ ለማጠር ወደ መቅደላ ጀርባ ተላኩ።

በሰላሴና ፋላ መካከል ባለው ሸለቆ የሚወስደው መንገድ በጣም ቀጥ ያለ ዳገት ነበር። ምናልባትም በየሶስት ጫማዎች ወደላይ ቀና እያለ ነበር የሚሄደው፤ ንጉሡ ራሳቸው እንዳሰሯቸው መንገዶች ሁሉ በጣም ቀጥ ያለ ዳገት ስለሆነ በቀላሉ ለመውጣት አይቻልም። ሰር ሮበርት ናፒየርና ረዳቶቹ እንደታዩ እኔም አብሬያቸው ዳገቱን መውጣት ጀመርኩ። አንድ ሺ የሚሆኑ ሰፍራዎች ላይ፣ ወደ ላይ ወደፋላ የሚወስደው መንገድ በቁጥጥር ሥር ውሏል። ሁሉም መኮንኖች እንደሚያምኑበት፣ ከዚህ ግዙፍ አለት ጀርባ፣ የሚመጣውን ጥቃት ለመከላከል፣ ጥቂት አውሮፓውያን ብቻ ማለቀመጥ የዘመቻውን ሁኔታ በእርግጠኛነት ይቀይረው ነበር። ወደላይ ለመውጣት ስንታገል፣ በአራት ትልልቅ የአለት ድንጋዮች መሀከል አለፍን፤ እንደገና ቁልቁል ትይዩ በሆኑ አለቶች መካከል ወርደን፣ ስንወጣ፣ ቀጥ ያለ፣ የሚንከባለሉ ድንጋዮች ፈጠጥ ያሉበት ዳገት ማየት ጀመርን። ከጋራው ወጣ ባለ መሄጃ ተጠማዘን ወደላይ ከወጣን በኋላ፣ ትንሽ ደልደል ባለ መንገድ ላይ እርምጃችን ቀጠልን። ይህም ወስዶ ከሌላ ቀጥ ያለ ዳገት ስር አደረሰን። ከዚያ በኋላ፣ እንደገና ወደላይ፣ ወደላይ፣ ቀጥሎም ወደላይ መውጣት ነበር። ይህም በእኩለቀን ፀሐይ፣ በፋላና በሰላሴ አህታማች ምሽጎች መሀከል ባለው ሸለቆ አፋፍ እስከንደርስ ነበር።

የምሽጎቹ እለቆች እጃቸውን ከለጡ በኋላ፣ በኮሎኔል ሎች የሚመራ የ3ኛው ቀላል ፈረሰኞች ቡድን፣ ምሽጎቹን እንዲይዝና ኗሪዎችን እንዲያስለቅቅ ተልኮ ነበር፡፡ የ33ኛው እግረኛ ክፍል ከፍታዎቹ ላይ ሲደርስ፣ ስድስት ኮምፓኒዎች ፈረሰኞቹን ለማገዝ ተመደቡ፡፡ ወደ ሰላሴ ራቅ ወዳለው ጠርዝ ተጉዘው ወደ ቀኝ ከታጠፉ በኋላ ከፍታው ላይ በመውጣት ወደምዕራብ እቅጣጫ ገሰገሱ፡፡ ሳንጃቸውን ወድረው፣ ወደ መንገዱ ሲቀጥሉ፣ የሚያገኟቸውን ያገሬው ተወላጆች ከምሽጉ እያስለቀቁ ነበር፡፡ ከዚያም የእንግሊዝ ጦር የቆመበት ቦታ ደረሱ፡፡ ከኮሎኔል ሎች ጋር፣ ካፔቴን ስፒዲ (ባሻ ፈለቀ) ነበር፡፡ እሱም በፈረሱ ላይ ሆኖ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሰ፣ እለቆችንና ዋና ዋና ሰዎችን ጉዳት እንደማይደርስባቸው እያግባባ ነገር ግን በእስቸኳይ ወደ ፋላ ሜዳ እንዲሄዱ እየመከረ ነበር፡፡ ለዎቹ እልፈው በሚሄዱበት የማለፊያው መውጫ ላይ፣ የወታደሮች ካምፓኒ ግራና ቀኝ በመቆም፣ እልፈው የሚወጡ ሰዎችን ትጥቅ ያስፈታ ነበር፡፡ ይህን ማለፊያ ወርደው ካለፉ በኋላ፣ ያገሬው ሰዎች የእንግሊዝ ወታደሮች ወደቆሙበት እርከን ያለበት ቦታ ብቅ እሉ፡፡

ወታደሮች በረዥም ሰልፍ ተሰልፈው ሲመጡ ሲያዩ፣ ተወላጆቹ በቅያሜ ቀጥ እሉ፡፡ ሆኖም በመረጋጋት፣ መንገዳቸውን ቀጥለው እርከኑ ቦታ ደረሱና ቆሙ፡፡ ያም፣ ወደታች ወደሜዳው መውረጃው መንገድ አስኪከፈትላቸው ድረስ ነበር፡፡ ፈረንጆቹ የማይጓዷቸው ወዳጆች መሆናቸውን እለቆቹ ሲረዱ፣ በወታደሮቹና በተጠረገው በሰላሴ በኩል ባለው ከፍተት ወረዱ፡፡ እዛም ሲደርሱ እልልታ ያስሙ ጀመር፤ የእንኳን ደህና ወጣችሁም ምልከት ሆነና ወደ ሰላሳ ሺ የሚሆኑ ሰዎች በደስታ ባንድ ላይ፣ ወደላይ፣ ወደ ሰማይ፣ ታላቅ የሆነ የህብረት ዜማ እንደሚሰማ አደረጉት፡፡

ወንዶች፣ ሴቶችና ህፃናት፣ እሽናፊዎችን ለመገናኘት ከሰላሴ ቁልቁል መውረድ ጀመሩ፤ በሁለቱ ምሽጎች መካከል ባለው ቦታ ላይ ያለውን የሰው ቁጥር በመጨመርም ሜዳውን ሞሉት፡፡

እኩለቀን ስለነበረ፣ እስካሁን ያላየነው ሞቃት ፀሐይ፣ በስማያዊው ግማሽ ከብ ሰፍራ በመሀል እናት ይወርድ ነበር፡፡

የአርምስትሮንግ መድፎችን የጫኑ ዝሆኖች ጋራውን መውጣት ሲጀምሩ፣ ወዲያውኑ፣ ፈረስ ላይ በተቀመጠ መኮንን ትዛዝ መሠረት፣ ወታደሮች ሰዎቹን መንገዳቸውን እንዲቀጥሉ በሳንጃቸው ያስገድዱ ጀመር፡፡ መንገዱም በሚጣደፉት ስደተኞች ተሞላ፡፡ ቀጥሎም ዳገቶቹ በነዚህ ሰዎች ጢም እሉ፡፡ በእልልታው ፋንታ፣ የለቅሶ ጩሁትና የሚያሳን የሀዘን እንጉርጉሮ ተተካ፤ በብዛት እየወረዱ ያሉትን ሰዎች ስናይ፣ እኛም ሳይቀር ነፍሳችን እስጨንቆን ነበር፡፡



የአፄ ቴዎድሮስ ቀሪ ሠራዊት ከመቅደላ ሲወጣ
(Roger Acton)



የእንግሊዝ ጦር እንቅስቃሴ ወደ መቅደላ

ካለንበት ኮረብታማ ቦታ ይህ ትዕይንት እያለፈ እያለ፣ ኮሎኔል ሎችና ካፒቴን ስፒዲ በሰላሴ ጠርዝ፣ ምሽጉን ዙሪያውን ባቀፈው መንገድ ላይ እይተጓዙ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ፣ መንገዱ ወደ መቅደላ ይወስዳል፡፡ ሰላሴና መቅደላን በሚያገናኘው የሰላምጌ ደልዳላ ቦታ ላይ የተወሰኑ ሰዎች ይታያሉ፡፡ እነሱም ፈረስ ላይ የተቀመጡ የጦር እሊቃ ልብሰ የለበሱ አቢሲኒያውያን ነበሩ፡፡ ከነሱ መካከል አንዱ፣ በለበሰው የሚያምር ልብሰና በነበረው ግርማ ጎላ ብሎ ይታያል፡፡ ይህ ሰው፣ ደማቅ የፈረሰ ልብስ የለበሰ ነጭ ፈረሰ ላይ ነው የተቀመጠው፡፡ የእንግሊዞች ፈረሰኛው ክፍል በሰላሴ ጎን መታየት ሲጀምር፣ ሰዎቹ ቀሰ ብለው ወደመቅደላ ተመለሱ፡፡ ሲመለሱ ግን እየተኮሱ ነበር፡፡

ሰላምጌ ሜዳው ላይ ከደረሱ በኋላ፣ የጫካ ድመት ዐይን ያለው ስፒዲ፣ የአቢሲኒያ ፈረሰኞች እዛ ቦታ የታዩበትን ምክንያት ያገኛል፡፡ እነሱም፣ ሰላምጌ ሜዳው ላይ ወደቀኝ በኩል ትንሽ ያርዶች ርቀት ላይ የነበሩ መድፎችን ለመውሰድ ነበር፡፡ ከፋላ በኩል፣ ወደነሱ አቅጣጫ ሁለት ጋዜጠኞችና ጥቂት የመድፈኛ መኮንኖች ነበሩ፡፡ የኮሎኔል ሎች ፈረሰኞችና ከፋላ በኩል የመጡት መኮንኖች የአፄ ቴዎድሮሰ መድፎች የተጠመዱበት ቦታ ላይ ተገናኙ፡፡ መድፎቹ ወዲያውኑ በቁጥጥር ስር ውለው የንግሥት ቪክቶሪያ ንብረቶች መሆናቸው ተነገረ፡፡ አብዛኞቹ መድፎች የብሪታኒያና የፈረንሳይ ስሪቶች ናቸው፡፡ ሌሎቹ ግን ቴዎድሮሰ በቀጠሯቸው ሩሲያኖች የተሰሩ ነበሩ፡፡

መቅደላ ከተመለሱ በኋላ ጥቂቶች የአቢሲኒያ ፈረሰኞች ጥቃት ለማድረግ ማሰባቸውን የሚሳይ እንቅሰቃሴ አደረጉ፡፡ ነገር ግን ስለ ውጤቱ እርግጠኛ ሰላልነበሩ፣ ወደመሃል መቅደላ መጋለቡን የመረጡ ይመሰላል፡፡ በቦታው የቆሙ፣ ቀራጥ የሆኑ፣ ወደመቶ የሚሆኑ የተወላጆቹ ወታደሮች አሉ፡፡ በዚህ ባለዝና ምሽግ ዳር ላይ፣ ጠቋቁር ጭንቅላቶች በመሰመር ብቅ ይሉና፣ አልፎ አልፎ ጠመንጃዎች በሚያሰተጋባ ጉልህ ድምፅ ሲተኮሱ ይሰማል፡፡

በድንገት፣ ፈረሰኞቹ፣ ወደ ስፒዲና መድፎቹን ወደሚቆጣጠሩ ጓደኞቹ ገሰገሱ፡፡ ከመሀከላቸውም ለየት ብሎ የሚታየው የነጩ ፈረሰ ልውላዊ ጋላቢ አብሮ ነበር፡፡ ሶለት መቶ ያርዶች እንደተጠጉ ሰዎቹ ቆሙ፡፡ ሰፒዲም፣ ያ ዘናጭ ነጭ ፈረሰ[136] ጋላቢ የአቢሲኒያው ንጉሥ ቴዎድሮሰ ራሳቸው መሆኑን ይገነዘባል፡፡

---

136 መቅደላ የነበረው የቴዎድሮስ ነጭ ፈረስ፣ ሀመር ይባል ነበር፡፡ ካፒቴን ስፒዲ፣ ባይከለከል ኖሮ የቴዎድሮስን የፍልሚያ ጥሪ ተቀብሎ ለመሄድ አስቦ ነበር፡፡

ካፒቴን ስፒዲ፣ ነጩ ፈረስ የተቀመጠው ሰው ጮክ ብሎ የተናገረውን ነገር ያረጋግጣል። ፈረሰኛው ፍልሚያ ነው የጠየቀው። "አትመጡም፣ ሴቶች ናችሁ? ጥቂት ፈረሰኞችን ለማጥቃት የምታወላውሉት?"

ይህ በርግጥ፣ ንጉሡ የት እንዳሉ እንዲታወቅ ስላደረገ፣ የእንግሊዝ ጦርን ከሃሳብ ነው ያዳነው። እንዲያውም፣ ለእንግሊዝ ጦር ያሚየረካ ነገር ነው የሆነው። ሁኔታውን ለመግለፅ ወደ ናፒየር መልከተኛ ተላከ። አብረዋቸው ከነበሩት እግረኛ ጦርና ፈረሰኞች ጋር በመሆን እንግሊዞቹን ለማጥቃት ሙከራ እስከሚያሳዩ ድረስ፣ ንጉሡ ለጠየቁት ፍልሚያ መልስም አልተሠጠም ነበር። ከዚያም፣ የተወሰኑ የ33ኛው እግረኛ ወታደሮች ቦታ እንዲያዙ ምልከት ተሠጣቸው። ወታደሮቹ፣ ከደልዳላው ቦታ ወደ ሸለቆዎች የሚወስዱ በግራ በቀኝም ያሉ መንገዶችን መቆጣጠር በሚያስችላቸው ሁኔታ ቦታ ያዙ። ሰላሴ ላይ ባንዴራቸውን ለመትከል በመዘጋጀት የነበሩ ሌሎች የ33ኛው ወታደሮች፣ የተማረኩ መድፎች ያሉበት ቦታ እገዛ እንዲያደርጉ ታዘዙ። ስድስት መድፎች፣ እርሳስ ተቀባብለው ስለነበር፣ ጥቂት መድፎች ወደ ተወላጆቹ አቅጣጫ ሲተኮሱ፣ ተወላጆቹ፣ በአፀፋው ያላነጣጠረ ተኩስ ጀመሩ። ይህ የሚፈለገውን ውጤት ነው ያስከተለው። ሰዎቹ ወዲያውኑ በሜዳው ላይ ወደ ነበሩ መጠለያዎች ጀርባ መሄድ ጀመሩ። እነዚህ መጠለያዎች፣ ቴዎድሮስ ሰዎቻቸውን ከደብረታቦር ሲያመጡ ለመቀበያ ብለው ያሠሩት ነበር። ተጨማሪ መድፎች ሲተኮሱ፣ ሰዎቹ ከተደበቁበት ቦታ ወጡ። የእንግሊዝ ጥቂት ወታደሮችና አብረዋቸው የነበሩ ጋዜጠኞች፣ ቴዎድሮስና ተዋጊዎቻቸው በፍጥነት ወደ መቅደላ አምባ ሲያፋገፍጉ ማየታቸው አርከቷቸዋል።

ነገር ግን፣ ቴዎድሮስ ከአለት ጉደባቸው ሆነው፣ ማንኛውም ወደ መቅደላ ጠጋ ለማለት የሚሞከር ሰው፣ ቀረብ ካለ፣ በማለም ጠመንጃ ይተኩሱ ጀመር። የ33ኛው እግረኛ ክፍልም፣ ከመቅደላ በሚመጣው፣ ገዳይና አስፈሪ የሆነ ተኩስ መረበሽ ጀመረ። ወዲያውኑ፣ አንድ የካምፕ ረዳት እየጋለበ፣ ከጄኔራል ስታቨሊ የተላከ የተኩስ እቁም ትዛዝ ይዞ መጣ።

የዚህ ተኩስ ድምፅ ደግሞ፣ ጄኔራል ናፒየርን ወደፊት እንዲመጣና ሁኔታውን እንዲቃኝ አደረገው። የ33ኛው ወታደሮች የእንግሊዚን ባንዴራ ሰላሴ ላይ እንዲተክሉ ታዘዙ። የ45ኛው ደግሞ ፋላ ላይ ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ ታዘዙ። የእንግሊዝ ባንዴራ ባንድ ጊዜ በሁለቱም ምሽጎች ላይ እንዲውለበለብ ተደረገ። ምንም ደም መፋሰስ ያልነበረበት ሁኔታ ቢሆንም፣ ክብር የሚገባው ስለነበር የአድናቆት "ቺርስ" ድምፅ እንዲሰማ አደረገ። እንደገናም፣ ዕይታው የሚመሥጥ ስሜት እንዲፈጠርም አደረገ። በዚህም፣ ሁለቱ የቴዎድሮስ ጠንካራ ምሽጎች ወደቁ።

በደቡብ በኩል የሚገኘውን፣ መሀል ላይ ያለውን ጉብታ እንደተሻገሩ፣ የመቅደላ ውነተኛው የጥንካሬ ገፅታ ወዲያውኑ መታየት ጀመረ፡፡

ሙሉ በሙሉ አለት ላይ የተፈጠረ፣ ሞለል ያለ ቅርጽ ያለው፣ ርዝመቱ አንድ ማይል ተኩል የሚሆን፣ ጎኑ ደግሞ፣ ከግማሽ እስከ ሶስትአራተኛ ማይል የሚሆን ቦታ ነው፡፡ ከሰላሴ በስተሰሜን በኩል ከሚያገናኘው ጠበብ ካለ ደልዳላ ቦታ ወደላይ 500 ጫማዎች ከፍታ አለው፡፡ አለቱ መቅደላ ነው፣ ላዩ ላይ ያለው ደልዳላ ቦታ ደግሞ ሰላምጌ ነው፡፡ መቅደላ፣ በምዕራብና በደቡብ ጎኑ፣ ከታች ከመልካጨሎ ሸለቆ በ2ሺ ጫማዎች ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡ በምስራቅ ጎኑ፣ በተደራራቡ ሶስት እርከኖች ግድግዳ፣ 600 ጫማዎች ወደላይ ከፍ ይላል፡፡ ከላይ እምባው፣ ሾጠጥ ያለ ቅርፅ ባላቸው ካሳር በተሰሩ የቤት ጣሪያዎች የተሞላ ነው፡፡ የእምባው ዳርቻ፣ በድንጋይ የተገነባ መከላከያ አለው፡፡ ከላዩ ላይ ደግሞ፣ ማስናከያ የሚሆን መከላከያ ተደርጎበታል፡፡ በሰላምጌ በፊት ለፊት በኩል ያለው ቦታ ግን፣ እጠር ያለ ግምብና ማሰናከያ አለበት፡፡ ይህም ዳገቱ አጋማሽ ላይ ነበር የተገነባው፡፡ በዚህ ቦታ በመሀሉ፣ ወደ ምሽጉ መግቢያ ብቸኛ በር የሆነ ማማ ተሰርቶበታል፡፡

የተወሰኑ ወታደሮች ፋላና ሰላሴን እንዲጠብቁ ከተመደቡ በኃላ፣ ሌሎች ሁሉም ወታደሮች የቴዎድሮስ መድፎች በተማረኩበት ቦታ፣ ወደ ሰላምጌ መጥተው እንዲሰባሰቡ ተደረገ፡፡

ሰር ሮበርት ናፒየር፣ የጠላትን ትክክለኛ ሀይልና የምሽጉን ሁኔታ ለማረጋገጥ በጣም ነበር የተጠበበው፡፡ መቅደላን ከአንድ አቅጣጫ ብቻ ማጥቃት ይቻላል ወይ? ይህም፣ ካለንበት ከሰላምጌ ፊት ለፊት የሚገኘውን ጎን ማለት ነው፡፡ እንደዛ ከሆን ደግሞ፣ ሠራዊቱ ከያዟቸው በላይ፣ ረዘምና ጠንከር ያሉ መሰላሎች ያስፈልጋሉ፡፡ ምንም እንኳን ከዚህ ከሚታየን የሰሜን ጎን ውጭ ሌላ ጎኖች ላይ ጥቃት ማድረግ ባይቻልም፣ ማንኛውም ወደ መቅደላ የሚወስዱ መንገዶች እንዲሸፈኑ ማድረጉ ታምኖበታል፡፡ ይህ ግዳጅ፣ 3ኛው ድራጎን ተብለው ለሚጠሩት ለአውሮፓውያኑ ፈረሰኞች ተሰጥቷል፡፡

የኮሎኔል ፔን የተራራ መድፈኞች ወይም ከባድ መሳሪያ ቡድን፣ ከተማረኩት መድፎች በቀኝ በኩል፣ ከመቅደላ 800 ያርዶች ርቀት ላይ መሳሪያዎቻቸውን እንዲጠምዱ ትዛዝ ተሠጠ፡፡ ከመቅደላ አንድ ሺ ያርዶች ርቀት፣ በሰላሴ ኮረብታ ላይ ደግሞ፣ የቲዊስ የተራራ መድፎች እንዲጠመዱበት ተወሰነ፡፡ የአርምስትሮንግ ከባድ መሳሪያዎች፣ በፋላና በሰላሴ መሀከል በሚገኘው ኮረብታ፣ ከመቅደላ 2500 ያርዶች ርቀት ላይ እንዲጠመዱ ተደረገ፡፡ ስለዚህ፣ የኮሎኔል ፔን መድፎችና የአርምስትሮንግ ከባድ መሳሪያዎች እንደግማሽ ከብ በሆነው ቦታ ላይ ዳርና ዳሩ ላይ ነው የተመደቡት፡፡ በዚህም፣

ከሁለቱ ጎን የሚተኮሰው ተኩስ መቅደላ ላይ እንደሚገናኝ ተደርጎ ነው፡፡ ባለ ሰምንት ኢንች ሞርታሮች ከአርምስትሮንግ መድፎች ግራ በኩል ተደግነዋል፡፡

ከቀኑ ስምንት ሰአት ሲሆን፣ የኮሎኔል ፔን መድፈኞች ለውጊያ ተዘጋጁ፤ ግልፅና ጎላ ባለ ድምፅ ተጀመረ፡፡ ሰር ሮበርት ናፒየር፣ ይህ ሁሉ ተኩስ ሲወርድ፣ የተከበቡት ሰዎች፣ ለመከላከል ምን አይነት እርምጃ እንደሚወስዱ ለማየት፣ ሰላሴ ኮረብታ ላይ ነበር፡፡

የሀውዜር ከባድ መሳሪያዎችን ተከትሎ፣ ሾል ያሉት የአርምስተሮንግ እርሳሶች፣ የሚንቀጠቀጥ ድምፅ ያለው የሙዚቃ ቃና እያሰሙ ወደላይ እየተሽከረከሩ በአየሩ ውስጥ ይሄዱና መቅደላ ላይ ሲደርሱ ይፈነዳሉ፡፡ ከዚያ ደግሞ የሞርታር እርሳሶች፣ የታዘዙትን ስራ ለመፈፀም የጠሉ ይመስል የሀዘን የመሰለ ድምፅ እያሰሙ፣ ነገር ግን፣ የማይቀረውን ዕጣ ለማድረስ ተከትለው ይወነጨፋሉ፡፡

ከዚያም ከባድ መሳሪያዎች ሥራ ጀመሩ፤ ሃያ የሚሆኑ፣ ሁሉም አይነት ካሊበሮች መቅደላ መግቢያውን ያጓሩበት ጀመር፡፡ ከነሱ ጋርም የእባብ ፉጨት ድምፅ ያላቸው ሮኬቶች ሲተኮሱ ይሰማል፡፡

በዚህ ሀይለኛ ድብደባ መሀል፣ አንዱ ጋዜጠኛ የቴዎድሮስን የመጨረሻ የእጅ ሥራ አይቼ እንደሆን ጠየቀኝ፡፡ እንዳላየሁት ስመልስለት፣ ላሳይህ በማለት ወደ ገደሉ ጫፍ እየመራ ወሰደኝ፡፡ በጣቱ እየጠቆም ቁልቁል በሚያመለክትበት አቅጣጫ ሰመለከት፣ ለዕድሜ ልክ መገለጥ ያለበት ሁኔታ ነው ያየሁት፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ አንባቢ ሆይ፣ አሰቃቂና ቀፋፊ ሁኔታ አልወድም፡፡ ነገር ግን ማሰብ ከተቻለ ወደ 308 የሚሆኑ ሰዎች አንዱ ባንዱ ላይ ተነባብሮ፣ ራቁት፣ አግርብረት በእግሮቻቸው ላይ እያሉ ተከምሮ ማየት፣ ይህን አሰቃቂ ሁኔታ በመግለፄ ይቅርታ ታደርጉልኛላችሁ፡፡

እንደዚህ ላለ ሰጀምላ ግድያስ በቂ ቅጣት መስጠት ይቻላል ወይ? የበቀል ፍርድ በሚሠጡ በሠለጠኑ ሰዎች ህግ፣ የሌላ ሰውን ሀይወት የሚነጥቅ ሰው ሕይወት ራሱ ይሰዋ ነበር፡፡ እንግዲህ 300 ሰዎች ሰሚገድል ሰው ምን ሊደረግ ይቻላል?

በቅርብ ጊዜ የተማረኩት ሰዎች እንደገለፁት፣ ቅጣቱ ሲፈፀም በቦታው ነበሩ፡፡ እስረኞቹ እጅና እግራቸው እንደታሰረ፣ በጎራዴና በጥይት እየተመቱ መሬት ላይ ይወድቁ ነበር፡፡ ብዙዎቹ እንደምንም ብለው በጉልበታቸው ተንበርክከው፣ ምህረት እንዲደረግላቸው ቢጮሁም ሰሚ አላገኙም፡፡ አንድ

ሳይተርፍ ሁሉም ተገደሉ፡፡ ይህ የሆነው እኛ ዳውንትና ደላንታ በደረስንበት ቀን በሚያዝያ 9፣[137] ነበር፡፡

ሰር ሮበርት ናፒየር፣ ከሁለት ሰአታት ድብደባ በኋላ፣ ተከላካዮቹ ደካማ ስለሚሆኑ፣ የሱ ወታደሮች ጥቃት ቢጀምሩ ከባድ ጉዳት እንደማይደርስባቸው ገመተ፡፡ ስለዚህ፣ የሮያል ኢንጂነሮችን፣ 33ኛውን፣ 45ኛወን እናም የንጉሡ የሚባለውን ጦር ለመጨረሻው ግዳጅ እንዲዘጋጁ ትዛዝ ሰጠ፡፡

የብሪታኒያ ከባድ መሳሪያዎች ተኩስ እንደጀመሩ፣ ከምሽጉ የሚተኮሱት ጠመንጃዎች አቁመው ነበር፡፡ በሩን ጥሰው እንዲገቡ የተመረጡት ወታደሮች በባታሊዮን ደረጃ ተሰልፈው በመቅደላና በሰላምጌ መሀል እሩብ ርቀት ላይ ተዘጋጅተዋል፡፡ በሜጀር ጎርደን ፐሪቻርድ የሚመሩት መሐንዲሶች ደግሞ፣ እንደ ጠብ አጫሪ ከባታሊዮኑ ፊት ለፊት ሆኑ፡፡ ተከታታይ የከባድ መሳሪያ ተኩስ ሽፋን እንዲሰጥ ከታዘዘ በኋላና ተኩሱም እየቀለጠ እያለ፣ ወታደሮቹ ወደ መቅደላ መራመድ ጀመሩ፡፡ የመቅደላ ግርጌ ሃምሳ ያርዶች ርቅት ሲደርሱ፣ ከባድ መሳሪያዎች ተኩስ አቆሙ፡፡ አሁን ግን የሮያል ኢንጂነር ክፍሎች በያዙት ስናይደር ጠመንጃ ተኩስ ከፈቱ፡፡ ከዛም 33ኛውና 45ኛው በያዙት ከኃላው ጥይት በሚቀባበልበት ጠመንጃ፣ በሚያስገርም ፍጥነት የጥይት ማዕበል ያወርዱ ጀመር፡፡ ያም ለአስር ደቂቃዎች ነበር፡፡

ቴዎድሮስና ታማኝ ተከታዮቻቸው ከባድ መሳሪያዎች ሲተኮሱ ተደብቀው መሽገው ነበር፡፡ ተኩሱ ሲያቆም፣ ቴዎድሮስ ራሳቸው እየፎከሩ ተነሱና ከተከታዮቻቸው ጋራ መግቢያ በሮችን ለመከላከል ሮጡ፡፡ ተሰልፎ የሚመጣውን ጦር ለማሸነፍ ወይም ለመሞት ቆርጦ በወሰነ ንጉሥ፣ የሚገባውን የውጊያ አቀባበል ለማድረግም ነበር፡፡

ቴዎድሮስ፣ ለሳቸው ምንም አይነት ምህረት አይደረግልኝም የሚለው ሀሳብ በልባቸው እሰካለ ድረስና ለእንግሊዞች ያላቸውን ስር የሰደደ ጥላቻ እንደያዙት ቢቀጥሉ ከበባው ሰኣታት ሳይሆን ወራት ድረስ በተራዘመ ነበር፡፡ አሁን ግን ምንም ማምለጫ አለመኖሩን ሲረዱ፣ ለሳቸው ሲሉ ደማቸውን ለማፍሰስ ከቆረጡት ታማኞቻቸው[138] ጋር በመሆን፣ በጥልቅ ድፍረት ወደ መግቢያው ማማና ዝቅ ወዳለው መከላከያ ከመጡ በኋላ ሰዎቻቸውን በየቦታው፣ ከፍተት ባለበት ቦታ መደቡ፡፡ ሲመለከቱ፣ የእንግሊዝ ወታደሮች በአራት ረድፍ ተሰልፈው፣ እየተኮሱ ወደ መግቢያው በር ሲያመሩ አዩ፣

---

137 (በምዕራፍ 11 ማስታወሻዎች)

138 ቴዎድሮስ፣ ወታደሮቻቸውን ሆነ አለቆችን፣ መሀላችሁን አንስቻለሁ ሄዱ በማለት ብዙ ወታደሮችን አሰናብተዋል፡፡ እነዚህ ግን ከንጉሡ ጋር ለመሞት ቆርጠው የወሰኑ ነበሩ፡፡

ከዚያም ሰዎቻቸው እንዲተኩሱ ምልክት ሲሰጡ፣ አነጣጥረው የሚተኩሷቸው ጥይቶች ብዙ ሰዎች አቆሰሉ፡፡ ነገር ግን ያሉበት ቦታ በእንግሊዞቹ ታወቀ፡፡

ወዲያውኑ፣ የእንግሊዞቹ የአፀፋ ተኩስ መግቢያው ላይ ተጠናከሮ፣ የሚጠረጠሩ መከለያ አጥሮች ላይም ተደረገ፡፡ መሽገው የተቀመጡት ሰዎች ከሚተኩሱት ጠመንጃ እንደ ከብ ሆኖ በሚወጣው ጭስ ያሉበት ቦታ ተለየ፡፡ በዚህ ጊዜ፣ የስቅለት ዕለት እንደሆነው ሁሉ፣ መብረቅና ነጎድጓድ ሲታይና ዙሪያውን ሲያነዝረው ለውጊያ አጃቢነት የሚስማማ መስሎ ነበር፡፡ ዝናቡም ደጎስ ባሉ ሞቃታ ጠብታዎች አናታችን ላይ በከብደት ይወርድ ጀመር፡፡ በዚህ በሚደባደብ የዝናብ ዶፍ መሀል፣ የማይበገሩ የሚመስሉት ወታደሮች፣ በርግጥም ያለምንም ፍርሀት ግስገሳቸውን ቀጠሉ፡፡ የያዙትን የስናይደር ጠመንጃ እየተኮሱ፣ በመቅደላ ዳር ዳር ላይ የሚጠረጠሩ በዚያም በዚህ ቀና ቀና ብለው የቆሙ አለቶችን በደንብ እያማተሩ ነበር፡፡

አሁንም በመሀንዲሶቹ እየተመሩ፣ አነዚያን ነብስ ገዳይ ሚሳይሎች (ሮኬቶች) በዳገቱ ላይ በተገኘው ቦታ ላይ እያረበረቡ ከማማው ስር ደረሱና ቆሙ፡፡

ለደቂቃ የሚሆን ጋብ ብሎ ነበር፡፡ ነገር ግን ወዲያውኑ ቀደም እያሉ የሚሄዱት መሐንዲሶች ላይ በደርዘን የሚቆጠሩ ተኩሶች ተከፈቱ፡፡ በዚህም ሜጀር ፕሪቻርድና ሶስት አራት የሚሆኑ መሐንዲሶች ቆሰሉ፡፡ በአፀፋው ደግሞ በእያንዳንዱ ተኩሰ በታየበት ቦታ ላይ ያነጣጠሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ተኩሶች ተተኮሱ፡፡ ሜጀር ፕሪቻርድና ወኔ የተሞላበት ሉተናንት ሞርጋን መግቢያውን ለመቆጣጠር እየሮጡ ወደማማው ሄዱ፡፡ ሲደርሱም በሩ ተዘግቶ አገኙት፤ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ማማ፣ ውስጡ አስር ጫማ ከፍታ ባለው የድንጋይ ካብ ተደፍኗል፡፡ ስለዚህ በውስጡ አልፎ ለመሄድ ቀላል አልነበረም፡፡

"በፍጥነት! ባሩዱን አምጡ!" ብሎ ሜጀሩ ጮኸ፡፡

ቀጥሎም፣ በመስመሩ ወደኋላ የተስተጋባው ድምፅ "በፍጥነት! ባሩዱን አምጡ!" "በፍጥነት! ባሩዱን አምጡ!" ነበር፡፡

ነገር ግን፣ ማን ነበረ ባሩዱን ማምጣት የነበረበት? ለምን እነዚያ ባሩድ የያዙ ሸራዎች ማቀጣጠያ ገመድ ላያቸው ላይ የታሰረባቸው ይህንን ቦታ ብትንትኑን ለማውጣት አልነበርም? ከባዶቹ መዶሻዎችስ የታሉ? በሩን ለመፈልቀቅና፣ መቆለፊያና ማጠፊያዎቹን መስበሪያ የሚሆኑት የብረት ሽብልቆችስ የታሉ? ግንቡ ላይ የተደረደሩትን የእንጨት መሰናከሎች መቁረጫ፣ መጥረቢያና መጋዞቹስ የታሉ? ግድግዳውን ለመናድና ለማፍረስ፣ ከበድ ያሉት መቆፈሪያዎችስ የታሉ? ግድግዳው ላይ ለመውጣት፣ ወይም

ከፍታ ያላቸው መሰናከያዎች ላይ መሻገሪያ የሚሆኑት የተደራረቡት መሰላሎችስ የት ይሆኑ? ያስተጋባው ድምፅ፣ "የታሉ? አሀ የታሉ?" ነበር፡፡ ለነዚህ አጣዳፊ ጥያቄዎች መልስ፣ አንድ ነፍስ እንኳን ትንፍሽ አላለም፡፡

የ33ኘው ወታደር፣ ማጉዋየር፣ የገደል ግድግዳውን መውጣት እችላለሁ ብሎ አሰቧል፡፡ ወጣ ወጣ ያሉትን ቦታዎች እየረገጠ፣ ሳያቋርጥ ወደላይ ከወጣ በኋላ፣ ዞር ብሎ፣ መግቢያ አገኘቻለሁ ብሎ ጮኸ፡፡ ከሰላምጌ በኩል በተደረገ ደከም ያለ የማበረታቻ ጩኸት በኋላ ፊቱን ወደ ግድግዳው አዞረ፡፡ በዚያን ጊዜ ግን ከኋላው የራሱ ሬጅመንት አባል የሆነው፣ ወታደር በርገን፣ እየተከተለው ነበር፡፡

ጠቅላላው ሬጅመንት፣ በደፋሮቹ ጓደኞቻቸው ምሳሌነት ተገፋፍተው፣ ቀጥ ያለውን ገደል እየተሸቀዳደሙ ይወጡ ጀመር፡፡ ትንፋሽ ቁርጥ ከሚያደርጉ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አናቱ ላይ ደረሱ፤ ከዚያም መቅደላ አናቱ ላይ የሚንቀሳቀሱ የሚጠረጠሩ ሰዎች ላይ ተኩስ ከፍተው ከመቅፀበት ፀጥ አደረጓቸው፡፡

በያዟቸው መሳሪያዎች፣ በእንጨት አጥሮቹ መሀል በመግባት፣ ወደላይ በማንሳት፣ ወዲያውኑ፣ ዝቅ ያለውን መከላከያ መሻገር ቻሉ፡፡ ከዚያም፣ መሬቱ ላይ ሲደርሱ ተበታትነው፣ በውጊያው ቦታ በብዛት የወደቁትን የሚዘገኑ አስከሬኖች እቋርጠው፣ 75 ጫማዎች ርቀት ላይ ወዳለው የመከላከያ አጥር ገሰገሱ፡፡

ወዲያውኑ በፍጥነት ሲተኩሱ ሰማን፡፡ ጠላት ሲንቀሳቀስ ሲል ስላገኙ በጥድፊያ ነበር የሚተኩሱት፡፡ ከዚያ ቀጥሎ፣ በሰደፋቸው በሮቹን ሲደበድቡ ሰማን፡፡ በሩን ለመሰበር ትልልቅ ድንጋዮች መወርወር ጀመሩ፤ አሁንም አሁንም በተገኘው ቀዳዳ ወይም ከፍተት ላይ ይተኩሳሉ፡፡ እነዚህን በስሜት የተሞሉትን የአየርላንድ ሰዎች፣ አጥር ሆነ በር፣ ግምብ ሆነ ድንጋይ፣ የእንጨት ከምር መሰናከልና ቀጥ ያለ አለት ቢሆን የሚያስቆማቸው አይነት አይደለም፡፡ በአጥሩ ውስጥ ላንጃቸው እንደዘለቀ፣ አጥሩ ከጥቅም ውጭ ሆነ፡፡ እናም፣ የቀረውን መከላከያ ሲዘሉ "ሁዛ!" "ሁሬፐ!" እና "ሁራ!"" የሚል ጩኸት እያሰሙ ነበር፡፡ ጠመንጃቻቸውን ደግነው ወደፊት እየገሰገሱ አቢሲኒያውያን ላይ በቅርበት ፊት ለፊት ሩምታ ተኩስ ተኮሱባቸው፡፡

ቀደም ብለው ግስገሳውን የጀመሩትን፣ ታምቡር መቺው ማጓየርና ወታደር በርገንን እንርሳ፡፡ ሁለቱ ሰዎች፣ አንዱ አንዱን በጥቂት ርምጃዎች እየተከተለ፣ ወደፊት፣ ወደላይኛው መሰናከል እየገሰገሱ ነበር፤ ቦታው ሲደርሱ ሰዎች እያነጣጠሩባቸው አገኙና ወዲያው በፍጥነት ያነጣጠረ ተኩስ ሲከፍቱ፣

ጥቂቶች አጥቂዎች ብቻ አመለጡ፡፡ ቀይ ኮት የለበሱ ሰዎች በቡድን ወደላይ ሲመጡ ሲያዩ፣ አጥቂዎቹ ወዲያውኑ በፍጥነት ነበር የሸሹት[139]፡፡

የላይኛውን መከላከያ ዘለው እንደተሻገሩ፣ ከገለባ ከምር አጠገብ በእጁ ሽጉጥ የጨበጠ አንድ ሰው ቆሞ ያያሉ፡፡ ሊተኩሱበት ሲዘጋጁ አይቶ፣ ወደ ገለባው ከምር ጀርባ ዞር ብሎ ሄደ፡፡ ከዚያም፣ ሁለቱ ወታደሮች፣ በግልፅ የተኩስ ድምፅ ሰሙ፡፡ የስናይደር ጠመንጃቸውን እንደያዙ ወደቦታው ሲሄዱ፣ ከገለባው አጠገብ ቆሞ የነበረውና ወደ ኋላ የተመለሰው ሰው መሬቱ ላይ ተዘርሮ ወድቋል፤ በቀኝ እጁ ሽጉጡን ጭምድድ አድርጎ እንደያዘ ህይወቱ እያለፈች ነበር፡፡ በአእምሯቸው ሽጉጡ የነሱ ምርኮ ነበር፣ ስለዚህ ምንም ሳያወላውሉ፣ የኛ ነው ያሉትን ሽጉጥ መንጨቀው ወሰዱ፡፡ ነገር ግን ሲመረምሩ፣ እጀታው ላይ ባለ የብር ልጥፍ፣ የሚከተለው ፅሁፍ ተፅፎበት አዩ፡፡

*ከንግሥት ቪክቶርያ*
*የታላቋ ብሪታንያና የአየርላንድ ንግሥት*
*ለቴዎድሮስ፣ የአቢሲኒያ ንጉሠ ነገሥት*
*ለአግሊጋይዋ ለፕላውደን ላሳየው ደግነት*
*ምስጋናዋን ለምግለፅ በመታሰቢያነት የተሠጠ*
*1854*


"ምን ታስባለህ፣ ፓት፣ ይህ ሰው፣ ቴዎድሮስ የሚባለው፣ ንጉሥ የሚሉት ይሆን?" ብሎ ማጓየር ጠየቀ፡፡

"ምናልባት፣ማክ፣ መናገር አልችልም፤ ሃምሳ አለቃው ፊቱን መቅደላ ውስጥ እስከሚያሳይ ድረስ እዚህ አጠገቡ ብንቆም ይሻላል፡፡ አች፣ እየመጣ ነው!" በርገን ነበር የተናገረው፡፡

እየገለገሰ የሚመጣውን የአየርላንድ ወታደሮች መስመር ሲያዩ፣ እነዚህ ሁለት ጀግኖች፣ ባርኔጣቸውን አውልቀው በራሳቸው ላይ እያውለበለቡ፣ ባልተለመደ ጠንካራ የሳምባ ህይል፣ በእንግሊሎ ሳከሰኖችን የጦርነት ጩኸት፣ "ሁራ!" በማለት ጓደኞቻቸውን ተቀበሏቸው፡፡

ሊዋጋ እንደሚዘጋጅ በሬ አንገታቸውን አቀርቅረው፣ "የመስፍኑ ጦር" የሚባሉት ወታደሮች ምንም ሳይጎድልባቸው ወደፊት መጡ፡፡ አርማ ያዡ

139 የአፄ ቴዎድሮስ ጠመንጃ ያዥ ወልደ ጋብር ለእንግሊዞቹ በሰጠው ቃል፣ ቴዎድሮስ ሰዎቻቸውን፣ መሀላችሁን አንስቻለሁ ሸሹ፤ እኔ ግን ለጠላት እጄን አልሠጥም ብለው ፈቃድ ስለሰጡ ነበር ሰዎቹ በፍጥነት የለቀቁት፡፡



የእንግሊዝ ጦር መቅደላን ጥሶ ሲገባ
(Roger Acton)

በመሀል፣ ረጋ ያሉት ወታደራዊ ሥርአት የያዙት መኮንኖች ከየኮምፓኒያቸው ኋላ ነበሩ:: ሁሉም በኩራት ወደፊት እየተራመዱ፣ በተጠንቀቅ፣ ለአፍታም ቢሆን የሚያሰጋቸው ካለ፣ እንደሚነድ እንጨት የሞቀ ነጭ ነበልባል በፍጥነት ለማፈንዳት ዝግጁ ነበሩ:: እያጣጣረ ያለው ሰው ወደ ወደቀበት ከፍት ቦታ ሲደርሱ፣ የሬጅመንቱ የመሀል ክፍል አቆመ::

በዚህ ጊዜ ዝናቡ አባራ፤ እናም ፀሐይዋ በሙሉ ጉልበቷ፣ በሰውየው፣ ግርማ ሞገስ ባለው መሰናበቻው ላይ ታንፀባርቅ ጀመር::

ትዛዝ ሲሰጥ፣ አርማ ተሸካሚዎች በጉጉት ወጡ፤ በድል አድራጊነት፣ በከፍታ፣ የሀሩን የተጠላለፈ መስቀል ያለበትን የብሪታንያን ግርማና ሀይል ሰንደቅአላማ በአካባቢው ካሉ ተራራዎች በላይ ማውለብለብ ጀመሩ:: ምልክትነቱም፣ ለያዙት ሰዎች፣ ጨካኙ ንጉሠ ነገሰት እንደተሸነፈና የሚኮራበት የመቅደላ ምሽጉም በእንግዶቹ እጅ እንደወደቀ ለማሳየት ነው:: ሰንደቅ አላማው በአየር ላይ ሲርገበገብና ሲውለበለብ፣ “የመሰፍኑ ጦር” ወታደሮች ባርኔጣቸውን እንዳወለቁ፣ በአንድ ላይ፣ በከፍተኛ የጋለ ስሜት፣ ድምፃቸውን “ቺርስ” በማለት አሰተጋቡ:: ድምፁም፣ ሰላምጌ ላሉና፣ ከታች 500 ጫማ ወረድ ብሎ ላሉ ሰዎች፣ እንደውቅያኖስ ማዕበል ጎላ ያለ ጉርምርምታ ነው ያሰማው:: ድምፁም ሰሊታወቀ፣ ከመቅደላ ተነሰቶ በቅብብሎሽ፣ ወደ ሰላሴ፣ ከዚያም ወደ ፋላ ሲሰማ፣ ግራጫ መልክ ያለው ቋጥኝ ደግሞ በማንጠር ታች ሸለቆ ድረስ አደረሰው:: በመጨረሻም፣ ሁለት ማይሎች ርቀት ላይ የሚገኘው የእንግሊዞች ካምፕ ድምፁን ተረከበው፣ የሁለ ገቡን "ሁራ"፣ በራሳቸው፣ ጉልበት በተመላበት ድምፅ አጠናከሩት:: ከወታደራዊው ባንድ የተለያዩ ሙዚቃዎች ገንፍለው መውጣት ጀመሩ:: 'God Save the Queen' የተባለው የእንግሊዝ ብሔራዊ መዝሙር የሙዚቃ ኖታዎች ከመቅደላ ገደሎች ላይ በጉልህ እየነጠሩ የሚያሰተጋቡት የህብረት ዜማ ሲሰማ፣ ለመቼውም ጊዜ ቢሆን እንደዚህ በሚያሰደንቅ ሁኔታ ተዘምሮ አያውቅም::

ጥቂት ያልታጠቁ አቢሲኒያውያን በሚሰማው ሙዚቃና ጫጫታ ተሰበው፣ በድፍረት፣ ሰንደቅአላማው በተራራው ነፋስ ወደሚውለበለብበት ቦታ ጠጋ አሉ:: መሬት ላይ የወደቀውን ያገራቸውን ሰው ሲያዩ፣ ጎንበሰ ብለው ተመለከቱና ወዲያውኑ የሚያሰፈራ ሀዘኔታ ከሚያሳየው ፊታቸው ጋራ ፈንጠር ብለው፣ በመደነቅ ድምፅ “ቴድሮሰ! ቴድሮሰ!” አሉ::

ቃሉ የእንዳንዱን ሰው ቀልብ ነው የሳበው፤ እና ሁሉም ወደ አሰከሬኑ መሄድ ጀመሩ:: የወደቀውን ሰው፣ በተወላጆቹ አጠራር “ቴዎድሮሰ” የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት! አንድ አፍታ እንኳን ለማየት እርሰ በርሰ እየተጋፉ ነበር::



የአፄ ቴዎድሮስ ፍፃሜ

እናስ ምን አዩ? ከሳ ያለው ያገራቸው ሰው ሰውነት፣ ከውስጥ ንፁህ የሰበሰ፣ በላዩ ላይ ግን በመለበስ ምክንያት አደፍ ያለና የተቀዳደደ ልብስ የደረበ ነበር።

በአቢሲኒያ፣ በጣም የሚደነቅ ጠየም ያለው ፊት፣ ብዙ የፈተና ሰአቶች ውስጥ ያለፈ የሚመስል ገፅታ አለው። አይኖቻቸው ምንም እንኳን አሁን የሞት ጥላ ቢጥልባቸውም፣ የሚከበሩና ሰውነት እልፎ የሚሄድ የትኩረት ሀይል የነበራቸው መሆናቸውን ያስመሰከራሉ። የታችኛው ከንፈር ንቀትን ለማሳየት በደንብ የተመቸ ይመስላል፤ አሁንም እንኳን ለእመል ያህል የንቀት ምልክት ይታይበታል። የመጨረሻውን ሰትንፋስ ሲያቃትቱ፣ ሁለት መሰመር የያዙ ነጫጭ ጥርሶች መታየት ጀመሩ። ከአፋቸው ጀምሮ፣ ሁለት ኀላ ያሉ መሰመሮች ከላይ ቀጥ ካለው አፍንጫቸው ጋር ይገናኛሉ። በፍጥነት ጥሏቸው እየሄደ ያለውን ትንፋሻቸውን በሚያጣጥሩበት ጊዜ፣ የአፍንጫ ቀዳዳዎች በጣም ሰፋ ብለው ይታዩ ነበር። ሰፋ ያለው ፊት፣ ፈጠጥ ያሉ የጉንጭ አጥንቶች ይታዩበታል፣ ግንባራቸው ኀላ ያለ ሆኖ፣ ቅንድባቸው ወጣ ያለ ነበር። ፀጉራቸው ከግንባራቸው ይጀምርና በሰስት ጉን ጉኖች ተከፍሎ ወደኋላ በአንገታቸው ጀርባ ይወርዳል። ወደኋላ እንደታየው፣ ፀጉራቸው የጥንካሬያቸው መመኪያ ነበር። ቁመታቸው አምስት ጫማ ከሰምንት ኢንች ሲሆን፣ የፈረጠሙ ጡንቻዎችና ሰፋ ያለ ደረት አላቸው። እነዚህ ገፅታዎች፣ ከፍተኛ የቆራጥነት ባህሪ ከወሳኝነት ወይም ጨካኝነት ጋራ ተቀላቅለው መኖራቸውን ያንፀባርቃሉ። ጨካኝነት የሚለው ሃሳብ እንኳን የተሰነዘረው፣ ብዙ ጭካኔ ያለባቸው ድርጊቶች ፈፅመዋል መባሉን በማስታወስ ነው። እንግዲህ ይኸው ቀሪ ሰውነቱን ያየነው ሰው፣ ሰዎች፣ የኢትዮጵያ አፄ ቴዎድሮስ፣ በምኒልክ ከሰለሞን ሀረግ የሚወለደ፣ ንጉሠ ነገሥት፣ የምድሩ ጌታ፣ የኢትዮጵያ ገዢ፣ የአፍሪካ መስራች፣ የኢየሩሳሌም ነፃ አውጭ ብለው የሚጠሩት ሕይወቱ እያለፈች ያለ፣ በራሱ እጅ ራሱን ገዳይ ነው።*

*(* በአስከሬን ምርመራው፣ በቀኝ አግራቸው ከተገኘው ቀለል ያለ ቁስል ውጭ በሌላ ፍንጣሪ እንዳልተጎዱ ሀኪሞቹ መዝግበዋል። ትናጋቸው ተሰብሮ፣ የውስጥ አፋቸው ጣሪያው ተለብልቧል፤ እናም በጭንቅላታቸው፣ በጀርባ በኩል ቀዳዳ ተገኝቷል። ሁሉም የሕክምና ሀላፊዎች ባንድ ላይ የሰጡት ውሳኔ፤ በአፋቸው ውስጥ የተተኮሰ ሽጉጥ ለሕይወታቸው ማለፍ ምክንያት መሆኑን ነው።)*

የስንት ዕደለ ቢስ ሰዎችን ሕይወት የነጠቀው፣ ቀዩ የቀኝ እጅ[140]፣ የራሱን፤ ሽፍታ ባለቤቱን ሕይወት መንጠቁ ተገቢ ቅጣት መሆኑ ነው!

---

140 ያገሬው ሰው "... ወንድ ያለራስዎ ገለውም አያውቁ" ብሎ ተቀኝቷል።





ኮኪት በር በእንግሊዝ ወታደሮች ሲጠበቅ

(ወደ መቅደላ መግቢያ በር፣ በፅሁፉ የተገለፀው የምሽግ መግቢያው የድንጋይ ካ
ያለው የእንጨት መሰኖክል በዚህ ፎቶግራፍ ተለይቶ ይታያል።)

በወደቀው አስከሬን ላይ፣ ውድቀቱን ለማብሰር በመጀመሪያ ጥላ ያሳረፈበት የቅዱስ ጊዮርጊስ አርማ መሆኑስ?

የአየርላንድ ወታደሮች፣ ሁለት እግሮቻቸውን ይዘው እየጎተቱ ወስደው ሽራው ላይ ካደረጓቸው በኋላ፣ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ አቃትተው የመጨረሻ ትንፋሻቸውን ተነፈሱ።።

ጥቅጥቅ ብለው ዙሪያውን በቆሙ ሰዎች ያልተለመዱ አስተያየቶች ይሰሙ ጀመር።። አንድ ሰው በላቲን ቋንቋ የሚከትለውን ቃል ሲናገር 'Sic semper tyrannis' ሌሎቹ ተቀብለው "አሜን አሜን!" አሉ።። ትርጉሙም "ሁልጊዜም ለአምባገነኖች ይሁን" እንደማለት ነው።። ሌላ የአየርላንድ ወታደር ደግሞ ከአሁን በኋላ ማንንም አያስቸግርም አለ።። ሌለው ግን፣ የጨዋነት ባህሪ ያለው ሰው፣ የተገለጠው ሆዳቸውን ሸፍኖ፣ እግሮቻቸውን ካስተካከለ በኃላ፣ ከንዶቻቸውን እጥፎ ደረታቸው ላይ አስቀመጠ።።

በአስከሬኑ ዙሪያ የሚሰበሰበው ሰው ቁጥር እየጨመረ ሄደ።። መኮንኖችና ወታደሮች አስከሬኑን ለማየት በችኮላ እየተጣደፉ ይመጡ ነበር።። የተለቀቁት ምርኮኞችም የሞተውን አሳሪያቸውን ለመሰናበት ይመጡ ጀመር።። ቴዎድሮስ መሆናቸውን ሲያውቁ፣ ስለሰውየው ማንነት የነበረውን ጥርጣሬ አስወገደው።። ቴዎድሮስ፣ የእንግሊዝ አልሞ ተኳሾች ለይተው እንዳይመቷቸው፣ ደማቅ ልብሳቸውን አውልቀው፣ ሌላ የማስመሰያ በመልበስ ነበር ሲዋጉ የነበሩት።። የጦሩ ጠቅላይ አዛዥም ከረዳቶቹ ጋር ሆኖ አስከሬኑን ለማየት መጣ፤ ነገር ግን፣ አንዳችም አይነት ቢሆን የሀዘን ቃል ለሞቱት ንጉሠ ነገሥት አልተነፈሰም።። ሌሎች ላይ ምህረት ያላያሳየ ለራሱ ሀዘኔታ አይገባውም።።

የመጨረሻዋ ሰአት፣ መሸነፋቸው አርግጠኛ መሆኑ አስኪታወቅ ድረስ፣ ህይወታቸውን አሳልፈው አልሰጡም።። ወደፊት በቀደሙት፣ ጠመንጃ ባነጣጠሩ ወታደሮች ቅፅበት ያለው ሞት መምጣቱን ሲያዩ ግን፣ ወደ ገለባው ክምር ጀርባ በመሄድ፣ ንግሥት ቪክቶርያ በስጧቸው ስጦታ፣ ሽጉጥ በአፋቸው በመጉረስ፣ ንጉሱ ራሳቸው ተኩሰው ራሳቸውን አጠፉ።።

አንቅስቃሴ እንዲጀመር ጥሩምባ ሲነፋ፣ ወታደሮቹ መሳሪያቸውን ትከሻቸው ላይ አጋድመው በሰልፍ በመሆን በጠባቡ የመቅደላ መንገድ መራመድ ጀመሩ።። ከኋላቸው፣ ዋናው ጦር አዛዥና ረዳቶቹ እየተከተሏቸው ነበር።። ረጅም በሆነው መንገድ ሲጓዙ፣ የሳር ከዳን ያላቸው፣ ባለ ጎጆ ጣራ የመካዘን ቤቶች በግራና በቀኛቸው በኩል ይገኙ ነበር።። ከዚያም፣ ወደ ደቡብ

አቅጣጫ፣ ሰፋ ያለ ገላጣ ቦታ ደረሱ፡፡ ምናልባትም፣ ቦታው ንጉሡ ለሰልፍ ወይም ለልምምድ ይጠቀሙበት የነበረ ቦታ ይሆናል፡፡

ወደ ዳር፣ ከዚህ ቦታ ወደላይ በኩል፣ ከጥቁር ድንኳኖች አጠገብ በርከት ያሉ የታጠቁ ያገሩ ተወላጆች ይታያሉ፡፡ እነዚህ ሰዎችም ወታደሮቹን ሲያዩ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ተኩሰ ከፈቱ፡፡ የ23ኛው ወታደሮች ደግሞ፣ ሜዳውን የሚሸፍን ያህል መስመር ሠርተው ሰዎቹ ላይ እየተኮሱ ወደፊት ይራመዱ ነበር፡፡ ከነዚህ በቀረጡ ወታደሮችና በማያባራው ጩኻኝ ተኩሶቻቸው ፊት ለፊት፣ የቴዎድሮስ የመጨረሻ ወታደሮች፣ በልጃቸው በደጃዝማች መሸሻ[141] እየተመሩ ቁልቁል በገደሉ ሸሹ፡፡

የአየርላንድ ሬጅመንት፣ በምስራቁ ጠርዝ በኩል ሲደርስ፣ የመቅደላ ምሽግ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር መሆኑን ለማሳየት፣ ሌላ ሰንደቅ አላማ ተተከለ፡፡ መሰፍኑም[142] ከበራሪ ወታደሮቹ ጋር ሆኖ፣ ይህ ሰንደቅአላማ ሲተከል የተሰማውን የቺርስ ድምፅና 'Rule Britannia' የተባለውን የወታደራዊ ማርሽ ሙዚቃ ሳይሰማ አይቀርም፡፡ በተቃራኒ በኩል ባሉ ተራሮች ላይ ያሉት የወሎ ኦሮሞዎችም ቢሆን ይህንን ድምፅ ሳይሰሙ አይቀሩም፡፡

ሰር ሮበርት ናፒየር እንደደረሰ ግን፣ ሙዚቃው ተቀይሮ 'See the Conquering Hero Comes' "ተመልከቱ፣ አሸናፊው ጀግና መጣ" የሚለውን መጫወት ጀመሩ፤ ተጨማሪ የደስታ ጩኸትና የብሔራዊ መዝሙር፣ የእርስ በርስ የእንኳን ደስ አለን ልውውጥ ጋር፣ መቅደላን ጥሶ የመግባት እንቅስቃሴ ተደመደመ፡፡

141 (በምዕራፍ ll ማስታወሻዎች)

142 ደጃዝማች ካሳ ምርጫን ለመጥቀስ ነው

# የምዕራፍ 11 ማስታወሻዎች

**ቁጥር 137፣** ስለዚህ የመጨረሻ የቴዎድሮስ ውሳኔ የራሳም ዘገባ ለየት ያለ ነው:: አንደኛ፣ በዛን ቀን የተገደሉ ሰዎች ቁጥር 198 ነው:: በሚያዝያ 8፣ ቴዎድሮስ 570 የአቢሲኒያ እስረኞቹ እንዲመጡ አስደረጉ፤ በመጀመሪያ 37 ታዋቂ የነበሩ ሰዎች እነ ክንቲባ ሀይሉና ባላምባራስ ተሰማን ጨምሮ ተለቀቁ:: ከነሱ ጋር 186 ሰዎችም ተፈቱ:: በሚቀጥለው ቀን ከጥቂት የፖለቲካ እስረኞች በስተቀር ሁሉም እንዲፈቱ ትዛዝ ሠጡ፣ ያን ቀን 95 ተጨማሪ እስረኞች ተፈቱ:: ነገር ግን የእግር ብረቱን መፍታታ ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ፣ ገና ያልተፈታላቸው እስረኞች መጮህና ማንጎራጎር ሲጀምሩ፣ ቴዎድሮስ ከቁጥጥር ውጭ ተናደዱና፣ በእግር ብረት የታሰሩትን አንድ ባንድ እያስጠሩ ጥፋታቸው እየተነበበ ቅጣቱ ይሰጥ ጀመር:: ቴዎድሮስ በቃ ሲሉ 198 የሚሆኑ ሰዎች ሀይታቸውን አጥተዋል:: ይህ ግድያ የተፈፀመው ከኛ ካምፕ ሁለት መቶ ያርዶች ርቀት ነበር ይላል ራሳም:: ሰውየው 300 ሰዎች ነው የሚለው ቁጥር ከዚህ በፊት የተገደሉትን ጨምሮ ካልሆነ በስተቀር በሚያዝያ ዘጠኝ በቅርብ ሁኔታውን የተከታተለው ራሳም የሚገልፀው እውነተኛ ይሆናል:: ቁጥሩ ማነሱ የደረሰውን ቅጣት አያቀለውም:: ያን ቀን ሌሊት ግን፣ ቴዎድሮስ ሲፀልዩ ነው ያደሩት:: በፀሎታቸውም ለሠሩት ሥህተት ይቅርታ ሲጠይቁ በጉልህ ይሰማ ነበር::

**ቁጥር 141፣** መሸሻ፣ ለዬ ቴዎድሮስ ከመጀመሪያ ሚስታቸው ከወለዷቸው ልጆች አንዱ ነው:: ሌላዋ፣ አልጣሽ ቴዎድሮስ ሰትሆን፣ ንጉሡ ለምኒልክ የዳሩላቸው ነበረች:: የነመሸሻ እናት፣ ገሡሡች፣ የእንግዳወርቅ ልጅ ሰትሆን፣ እንግዳወርቅ ደግሞ ከቴዎድሮስ ጎን እስከመጨረሻው ድረስ ተዋግተው ከሞቱት የቴዎድሮስ ሰባት አለቆች አንዷ ናቸው:: እንግዳወርቅና ቴዎድሮስ ከሽፍትነት ጊዜ ጀምሮ ነው የሚተዋወቁት:: ጋብቻው የፈረሰው፣ ቴዎድሮስ፣ እቴጌ ተዋበች አሲን ለፖለቲካ ሲባል እንዲያገቡ በተዋበች እያት በመነን ሲጠየቁ ነው:: ጋብቻው የፖለቲካ ቢሆንም፣ ተዋበች፣ በዘመኑ ቆንጆ ተብላ የምትደነቅ ሴት ከመሆኗ በተጨማሪ፣ በሁለቱ መሀል ፅኑ ፍቅር ነበር:: ካሳ ላይ በተደረገው፣ በተለይም በእቴጌ መነን (የተዋበች አያት) ንቀት ምክንያት፣ ሚስትየዋ ተዋበች ነች፣ አታሰድቡኝ፣ ብላ በወላጆቿ ላይ እንዲነሱ ያደረገቻው:: ደጃች ካሳ በሽፍትነት በየቦታው ሲዘዋወሩ፣ ተዋበችን ደብቀው ያስቀመጡት የቴዎድሮስ ወዳጅ ኢይከል ኮልባ ይባሉ ነበር::